# ECIC
## Ethio Cult Info Center
DEFENDING THE DEFENCELESS

Web seite http: / /www.saveethiopians.net

<u>ከኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል</u>

## ለኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ክፍሎች የቀረበ ህዝባዊ የትብብር ጥሪ

ECIC-o8/6___________________________

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊ ወንድምና እህቶች ::

ሰላም ለእናንት ይሁን ባላችሁበት:-

የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል Ethiopian Cult Information Center(ECIC ) ድርጅት በህጋዊነት ደረጃ በአሜሪካና አውሮፓ ከተቋቋመ ሁለት አመት የሆነው ሲሆን በዚህ ሁለት አመት ውስጥ በተለያዩ ሚዲያዎች ህዝብን በሀይማኖት ሽፋን የስህተት አጀንዳን ይዘው የሚንቀሳቀሱ በምእራቡ አለምና አገር ውስጥ በመጥፎ ድርጊታቸው የታወቁ ጎጂ አምልኮ መሳይ ድርጅቶችን እውነተኛ ማንነት በምእራቡ አለም ያላቸውን ምንነት መረጃ በማቅረብ በውጪና በአግር ውስጥ ለሚገኘውና ለኢትዮጵያዊው ህብረተሰብ ሲያስተምር ቆይቷል:: ህንንም የጋራ የሆነ አደራና ህዝብን የማሳወቅ ራእይ በተለይ በውጪ በሚገኙ አኢትዮጵያዊያን ሚዲያዎች ከድርጅታችን ጋር በመተባበር ኢትዮጵያውያን ሚዲያዎች (ድህረ ገጾች መጽሄቶች....ወዘተ) ያደረገኡት ታላቅ ህዝብን የማስተማር ተጋድሎ የሚዲያዎችን ህዝባዊነት ብቻ ሳይሆን ህዝባዊ አደራ የሚወጡ መሆኑን አሳይቷል::ለዚህም ከታች የሚገኙትን የድህረ ገጽ አድራሻዎች በዋቤ መልኩ መጥቀስ ለእናንተም በውጪ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊ ሚዲያዎች ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት ያደረጉትን ታላቅ ተጋድሎ ያሳያል ብለን እናምናለን::

http://www.ethiolion.com/113007_Menafikan.html
http://www.ethioguardian.com/comment.php?comment.news.1149
http://amelna.blogspot.com/2007/08/ethiopians-pentes-21st-century.html
http://www.debteraw.co.uk/Article-u-tube-invasion.htm

በይዘቱ ለአገራችን ለመጀመሪያ የሆነውን የዜጎችን ደህንነትና መብት ለማስጠበቅ ለማንኛውም ክፍል ያልወገነ የኢትዮጵያዊያን ስለ ጎጂ እምነቶች መረጃ መአከል Ethiopian Cult Information Center(ECIC ) ወደ ህይወት መጥራት ያስፈለገበት ምክንያት ከዘመናት ወደ ዘመናት በመጤና ጎጂ ኍላ ቀር አምልኮ ቡድን መጠሪያ ስም ሽፋን ተጠቂ የሚሆኑ ወገኖች ችግራቸው በመጤና ጎጂ ኍላ ቀር አምልኮ ቡድን መጠሪያ ስም ሽፋን የሚፈጸምባቸው ወንጀል ህዝብ አንደሌላው አለም የሚያውቅበት መንገድ ባለመኖሩ ተሸፋፍኖ በመቅረቱ ብዙዎች ተጠቂ ሲሆኑ ታይተዋል::

ተከላካይና ጠባቂ የሌላቸውን ሕፃናት እንዲሁም በኑሯቸው ችግርና ተስፋ መቁረጥ በርሃብና በስራ አጥነት የሚጉላላውን የህብረተሰብ ክፍል ባንዳንድ ጥቃቅን ማባበያ የህብረተሰቡን አምራችና ታዳጊ ሕጻናትን አይምሮአቸውን በማላሸቅ ለሐገርና ለወገን እድገት እንዳያስብ የከንቱ እምነት ሰለባ እንዲሆን በውጪ ሀይሎችና በተላላኪዎቻቸው ተደርጓል:: በስልጣን ላይ ያለውም መንግስት ይህንን እያየ ዝም ማለቱ ሕዝቡ ባልባሌ ባህልና ኀይማኖት ተብትቦ አይምሮው ደንዝዞ በመያዙ በሕዝባችን ብሩህ ሕይወት በአገር ደህንነትና እድገት ላይ ይህ ነው የማይባል በደል እየተፈጸመ ይገኛል: ይህ የባእዳን ማደንዘዣ ሕዝቡን ተብትቦ በመያዙ አገራችን ልትወጣው ወደማትችል ባርነትና የባህልና የህብረተሰብ ድቀት እንድትወርድ በደል እየደረሰ ነው:: ይህ ሀይማኖት ወይንም እምነት ሳይሆን ህብረተሰቡን ለባዕድ አገርን ለውርደት በመዳረግ ደካማና የተኮላሸ ህብረተሰብ ለማድረግ በምእራባውያን አቀንቃኝነት ባገራችን

ኢትዮጵያና በሕዝባችን የሚያናደርሱት ታላቅ በደል ዛሬ ታግለን ከአገራችን ምድር በማስወጣት ወደመጣበት ባህር ማዶ ተመልሶ እንዲሄድ ማድረግ ካልቻልን ነገ ላገርና ለወገን ተቆርቋሪ ዜጋ ይኖራል ማለት አዳጋች ነው:: ስለሆነም ይህ በህብረተሰባችን ላይ የሚያደርሱትን ኢሰብአዊ ድርጊት እንደሆነ ታውቆና ታምኖበት አገርንና ወገንን ለማዳን ሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሚዲያ ክፍሎች ይህንን አድራጎት በጥብቅ በማውገዝና ህብረተሰቡንም በማስተማር የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ሊተባበር ይገባል::

ይህንን አለማወቅ በህብረተሰባችን ውስጥ ለመግታትና ወንጀል እንጂ ከአምልኮ ጋር ግንኙነት የሌለው ድርጊት መሆኑን ለማሳየትና የወደፊቱ ትውልድም አምልኮን እንደማስክ እየተጠቀሙ የተለያዩ ወንጅሎችን በዜጎች ላይ የሚፈጸሙ ድርጅቶችንና አምልኩኝ ባዮቻቸውን ለይቶ እንዲያውቅ መረጃዎችን Ethio-Cult Information Center http://www.saveethiopians.net ያቀርባል::

ውድ ኢትዮጵያዊ የሚዲያ ክፍሎች ዜጎችን(ግለሰቦችን) በአምልኮ መሰል ስም ቀርቦ ጥቂቶችን ከህዝብ ነጥሎ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በሌላው አለም (International Standard) ተቀባይነት በሌለው መልኩ በማስቸገርና ብዙዎች ደካማ ዜጎቻችን ከሚደርስባቸው ስቃይ ማለትም ጤናቸውን On/off እንደሚል መብራት በማሳመምና በተጨባጭ በድህረ ገጻችን የታየ ደም አስከመትፋት: ሽባ እስከመሆን ድረስ በአምልኮ ስም ቀርቦ በማሰቃየትና በስራቸውና በትዳራቸው ሰላምን በማሳጣት በምድር ህይወታቸው ተስፋ እስኪቆርጡ ድረስ በማሰቃየት የሚረዳኝ ዜጋ የለም ብለው ችግራቸውን ለህዝብ መናገር ፈርተው የሚሰቃዩበትንና የምድር ህይወታቸውን እንደሮቦት ዜጎችን በአምልኮ ስም የመጠቀሚያውን ሲስተም በማጋለጥና ለሌሎች ለትምህርትና ለጥንቃቄ እንዲሆን ላላወቁ ቤተሰቦቸ : ወዳጆችና ለመገናኛ ብዙሀን (ጋዜጣና መጽሄት ኢንተርኔት የመሳሰሉትን ) የኢትዮጵያዊያን ስለ ጎጂ እምነቶች መረጃ መአከል (Ethiopian Cult Information Center( ECIC) http://www.saveethiopians.net ድህረ ገጻችን በማሳውቁ ይተባበሩን ::

በዚሁ አጋጣሚ ምን ያክል ዛሬ ኢትዮጵያውያኖች በውጪ ሀይሎች በሚመሩ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች እንደተጠቁ ክብራቸው እንደተነካና ብዙ ገና ስለእነዚህ ጎጂ አምልኮ ቡድኖች ያላወቁ ቡድኖች በእነዚህ ቡድኖች ማታለል ሊጠመዱና ነገ ተጠቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማየት ይችሉ ዘንድ እነዚህ ቪዲዮዎች ከኢንተርኔት ላይ እንዲመለከቱ አደራ እንላለን:.

**http: / / www.youtube.com / watch?v=VD9ZKgUR25M**
**http: / / video.google.de / videoplay?docid=5371941839083108494**
**http: / / video.google.de / videoplay?docid=-8155637464973550729**
**http: / / www.myjesussaves.com / T8.html**
**http: / / ex-pentecostals.org /**
**http: / / www.bible.ca / tongues-encyclopedia-pentecostal-preachers.htm**

ከዚህም አንጻር ህዝባዊ ሚዲያዎችን እርዳታ በመጠየቅ ድህረ ገጻችንን ለህዝብ ማሳወቁ አስፈላጊ ነው ብለን ለጋራ ጉዳይ ትብብራችሁን እንጠይቃለን:: የድህረ ገጻችንን አዳራሻና ስለድህረ ገጻችን መጠነኛ ሪፖርት በመዘገብ በጋዜጣችሁ በመጽሄታችሁ ላይ በሚመቻችሁ መልክ በማተም ያላወቀ ህዝባችንን ህዝብ ስለዚህ ነገር ጥንቃቄ እንዲያረግ በማሳወቁ ተባበሩን:: ውለታውን ሳይማር ያስተማረን ህዝብ አምላክ ሁላችንንም ይክፈል
የኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል (Ethiopian Cult Information Center( ECIC) አዳራሻ http://www.saveethiopians.net

ECIC
Ethio Cult Info Center
DEFENDING THE DEFENCELESS

Web seite http://www.saveethiopians.net

አገራችን ኢትዮጵያን ሰላም ያቆይልን

የድርጅቱ የህዝብ መገናኛ ክፍል
<u>ከኢትዮጵያ የጎጂ አምልኮ መካላከያና መረጃ መዐከል</u>
Ethiopian Cult Information Center (ECIC )
ይጎብኙ ድህረ ገጻችንን http://www.saveethiopians.net

Contact: ecic-publicrelation@saveethiopians.net or ecic-editorial@saveethiopians.net